

# ሰዎች ምን ይላሉ?!

ቅንብር ፡ አሥራደው (ከፈረንሳይ)  ክፍል 1

«እንኳን አደረሳችሁ»! ለሚለው የመልካም ምኞት መግለጫ፤

የተሰጠው መልስ፤ «አልደረሰኩም ገና»! የሚል ሲሆን፡ ቋጠሮው፤

በጥላቻ መንፈስ - እያለን በእሮሮ፤
ሰለባተ ብቻ - መስከረም ቀን ቆጥሮ፤
አንድነት ሳይጠባ - ወር ብቻ ቆጥራችሁ፤
«እንኳን አደረሰሽ «እንኳን አደረሰህ» ! አትበሉኝ እባካችሁ !!

እቴጌይት (ከዋርካ ድረ ገጽ)

## እኔ ምን አገባኝ ?!

እኔ ምን አገባኝ?! የምትሉት ሐረግ፤
እሱ ነው አገሬን ያረዳት እንደ በግ፤
የሚል ግጥም ልጽፍ ብድግ አልኩኝና፤
ምን አገባኝ ?! ብዬ ቁጭ አልኩ እንደገና::

ከኑረዲን ኢሳ

## ፈጣሪና አበሾች

አበሾች ተጣልተው አበሾች ሊያስማሙ፤
በይቅር ለእግዚአብሔር ጉንጬ ሊያሳስሙ፤
ዋሽቶ ማስታረቅን መልካም ነው ይላሉ::
መዋሸት ሃጢያት ሲል የመጽሐፍ ቃሉ፤
ፈጣሪና አበሾች እዚህ ጋ ተጣሉ::

ሰንታየሁ አበበ (ከጣይቱ ማዕከል)

EthioLion.Com